**“ቤቴ የፀሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተፅፎአል እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችሁት አላቸው።” ማቴ. ምዕ፣21ቁ.13**

## ምኩራብ

መቅደስ መልካም ስፍራ
የፅድቅ በር መግቢያ
ይቅር መባባያ መታረቂያ
ውዳሴው የሚሰማባት
ዝማሬው የሚያስተጋባባት
ንፁህ ዘር የሚዘራባት
መንፈስ አዳሽ ልዩ ቦታ
ሰላም ያለባት የውስጥ እርካታ
እውነተኛ ደጅ የሰዎች አለኝታ
የግሩማን መላዕክት መመላለሻ
የቅዱሳን ፀሎት ማሳረጊያ
ተለውጣ ቢያያት የበጐች እረኛ
ምሳሌ የማይገኝለት እውነተኛ ዳኛ
ጅራፍን አበጀ ሊታደጋት ሽቶ
መቅደሱን ሊያጠራ
ቤቴ የፀሎት ቤት ትባላለች ብሎ።
ምነው ቤቴን ማርከሳችሁ
ቅሚያና ዝርፊያ መልመዳችሁ
ሰላሜን መናቃችሁ
ከቶ እንዲህ መድፈራችሁ
በከንፈር ብቻ አክብሮ
ልባችሁ ግን ከኔ ርቆ
ምናምንቴዎች ሆናችኋል
እምነታችሁን ትታችኋል
ማስተዋል ተስኗችኋል
ፌዝና ቧልት ለምዳችኋል
ቁምነገርን ጠልታችኋል
ሳቅና ቀልድ አብዝታችኋል
ትዕዛዜን አፍርሳችኋል
ሕጌንም ጥሳችኋል
እኔኑ ሰርቃችኋል
ማዳኔንም ክዳችኋል
ክንዴንም ረስታችኋል
እኔም እላችኋለሁ
ዕጣናችሁን ተፀይፌዋለሁ
መስዋዕታችሁንም ቸል ብየዋለሁ።
ምነው ቤቴ ተለወጠ
ራሱን ወድዶ ሌላውን ጣለ
እየቀማ እያታለለ።
እስከመቼ እንዲህ ሊኖር
እውነት ተጥላ ሐሰት ነግሳ
አንዱ በአንዱ ላይ እየተነሳ
አሳልፎ ሲሰጣጡባት
ትህትና ጠፍቶ ሲናቆሩባት
መቅደሴን መነታረኪያ
የጭቅጭቅ መናኸሪያ
የትዕቢት ቃል መነጋገሪያ
መልካሙን ሰው ማደናገሪያ
እንዳይለማበት ማሰናከያ
መሸጫ መለወጫ
የወንበዶች ዋሻ
መፈንጫ መራገጫ
ቤቴንማ እንደዚህ አድርጋችሁ
እንዴት ይቅር ልበላችሁ
ይህንማ መቼ ፈቅጄ
ጅራፍ ይዣለሁ ይኸው በእጄ
ቤቴን ላፀዳ ተሰናድቼ።
በሉ ንሡ ከዚህ ውጡ
መቅደሴን አታውኩ
ጀርባ ጀርባቸውን እየገረፈ
መሸጫ ገበታቸውን እየገለበጠ
ከመቅደሱ ውጪ አሰወጥቶ እያባረረ
ስለቤቱ ቀናተኛነት አበክሮ እየተናገረ
እነሆ ቤቱን አስከበረ
ቤቴ የፀሎት ቤት ትባላለች እያለ።

ከኃይለመስቀል ተስፋዬ
ለንደን (የካቲት 9/2004)